

# ዳንኤል

* ንጉስ ብልጣሶር 1000 ለሚያህሉ ታደሚዎቹ ግብዣ አዘጋጀ። ታዲያ ለእነኝሁ እንግዶቹ ልዩ የመጠጫ ፅዋዎች እንዲመጡላቸው አዘዘ። እነኝህ የመጠጫ ፅዋዎች በኢየሩሳሌም ከሚገኘው ከእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ በብልጣሶር አባት ተዘርፈው የመጡ ናቸው። በእነኝህ ፅዋዎች እየጠጡ ጣኦታትን ማወደስ ተገቢ አልነበረም። እግዚአብሔር በዚህ እጅግ በጣም አዘነ።

* ታዲያ በድንገት አንዲት እጅ በግድግዳው ላይ መፃፍ ጀመረች። ንጉሱ እጅግ ደነገጠ። እግሮቹም ተንቀጠቀጡ። ጠቢባኑን ሰበሰበና የቃላቱን ትርጉም እንዲነግሩት ጠየቃቸው። ነገር ግን አልቻሉም። ንግስቲቱም በግዛቱ ውስጥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበትና ይህንን ነገር መፍታት የሚችል ሰው እንዳለ ለንጉሱ ነገረችው። ይህም ሰው ዳንኤል ነበር።

* ዳንኤል ቃላቱን በትክክል ተናገረ። እንዲህም አለው “ እግዚአብሔር በአንተ አልተደሰተም። ከእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ በተዘረፉ ፅዋዎች እየጠጣህ ጣኦታትን አወደስክ። በሚዛን ተመዘንክ ቀልለህም ተገኘተሃል። ግዛትህ ይከፈላል። አንተም ትሞታለህ።”

* ዳንኤል የተናገረው ሁሉ በዚያን ምሽት ተፈፀመ።

* ከብልጣሶር ቀጥሎ የተነሳው ንጉስ ዳሪዮስ ይባላል። ታዲያ ይህ ንጉስ ዳንኤልን በጣም ይወደው ነበር። በዳሪዮስ ግዛት ውስጥ ዳንኤልን የማይወዱት ክፉ ሰዎች ነበሩ። እርሱን የሚያጠፉበትን መንገድ ይፈልጉ ነበር።

ስለዚህ ዳሪዮስን ሕግ እንዲያወጣ ያግባቡታል። ይህ ሕግም ለተከታዮቹ 30 ቀናት ማንም ሰው መፀለይ የሚገባው ለዳሪዮስ ብቻ እንደሆነ ይገልፃል። ከዳሪዮስ ውጪ ለሌላ አምላክ ወይንም ለእግዚአብሔር የሚፀልይ ቢገኝ ወደ አንበሶች ጉድጓድ ውስጥ እንዲጣል ተወሰነበት። ሆኖም ዳንኤል እንደለመደው ወደእግዚአብሔር መፀለዩን ቀጠለ። እነኛ ክፉ ሰዎችም ዳንኤል ወደ እግዚአብሔር እየፀለየ እንደሆነ ነገሩት። ስለዚህ ንጉሱ በሕጉ መሠረት ዳንኤልን በአንበሶች ጉደጓድ ውስጥ እንዲጣል ማድረግ ነበረበት።

* እግዚአብሔር ግን ዳንኤልን ከአንበሶች አዳነው። በተከታዩ ቀንም ንጉስ ዳንኤልን በአንሶች ጉድጓድ ውስጥ በደህና አገኘው። እግዚአብሔር የአንበሶችን አፍ ዘጋ። በሁኔታው የተደሰተው ንጉስና ሕዝቡ እግዚአብሔርን ማምለክ ጀመረ።

. ይህ የዳንኤል ታሪክ የሚገኘው በብሉይ ኪዳን በመፅሐፈ ዳንኤል በምዕራፍ 6 ነው።